

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከጁን 11-20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ እንዲሁም

## ከጁን 21-30/2025 እና ከጁላይ 1-10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2025

አዲስ አበባ


## 1. እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በመጨረሻዎቹ ሰባት ቀናት ላይ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በባህር ዳር 21፣ ደብረ ማርቆስ 25፣ ቢሾፍቱ 24.2፣ ጎንደር 29.4፣ ጎሬ 23.3፣ 21.7፣ ነቀምት 27.3፣ 54.5፣ 35.3፣ አቦቦ፣ 38፣ አይራ 28.5፣ 20.6፣ 64.6፣ 32፣ አማን 53.4፣ 43.4፣ 30.8፣ አንገር ጉቲን 30.4፣ 23.2፣ 59፣ አርጆ 24.2፣ 28.6፣ አይከል 25.3፣ በደሌ 24፣ 21.3፣ 37፣ ቦሬ 50.9፣ ቡለን 24፤ ቻግኒ 23.2፣ 50.6፣ 31.7፣ ጨዋቃ 38፣ 22፣ 32፣ ጭራ 25.4፣ ዳንግላ 20.1፣ ደባርቅ 33.1፣ ደምቢ ዶሎ 35.2፣ 25.2፣ ፉጊዶ 23፣ 37፣ 32፣ ጋምቤላ 34.5፣ 32.2፣ ጋቲራ 29.3፣ 25.7፣ 34.6፣ 26.4፣ ጊዳ አያና 23.5፣ 62.3፣ ሆሳዕና 22.4፣ እምድብር 26.1፣ ካቺሴ 40፣ ማንኩሽ 23.5፣ 30፣ 60.4፣ 30፣ 50.6፣ 36.4፣ መተማ 42፣ አዳማ 29.4፣ ነጆ 21፣ 56.8፣ ሰኮሩ 41.2፣ ሻዉራ 20.9፣ ሻምቡ 27.4፣ ሽርቆሌ 43.4፣ ቴፒ 55.8፣ ወራቤ 23.2 እንዲሁም ወላይታ 21.9፣24.3 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ25 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 41.2 - 64.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል አየሁ፣ ጊዳ አያና፣ ማሻ፣ አንገር ጉቲን፣ ነጆ፣ ቴፒ፣ ነቀምት፣ አማን፣ ቦሬ፣ ቻግኒ፣ ማንኩሽ፣ ሰኮሩ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ምስል፡1 ከጁን 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታ፣ ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ21-252 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ::




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር


በሌላ በኩል በሰመራ፣ በገዋኔ፣ በመተሃራ፣በአዋሽ አርባ፣ በአይሻ፣ ጭፍራ፣ በመተማ፣በድሬ ዳዋ፣ ዳሊፋጊ፣ በፉኙዶ፣ በጨፋ፣ በሻዉራ፣ በማጀቴ፣ በኑራ ኤራ፣ በማይጨዉ፣ በመኢሶ፣ በጎዴ፣ በባቲ፣ በቀበሪዳሀር፣ በአቦቦ፣ በጋምቤላ፣ በአቦምሳ፣ በኮምቦልቻ፣ በአይደር፣ በሸርቆሌ፣ በስሪንቃ፣ በአለም ከተማ፣ በአዳማ፣ በሽሬ እና በቴፒ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 33.4 እስከ 45.8 ዲግሪ ሴልሸየስ ተመዝግቧል፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የጁን ሁለተኛው አስር ቀናት በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት በአብዛኛው የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የነበረ ሲሆን የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው። ይህም ሁኔታ አስቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ  የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችና ፍሬ በማፍራት ላይ ለነበሩ የበልግ ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ ቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም በጁን ወር ለሚዘሩ የተለያዩ የመኸር ሰብሎች ለማሳ ዝግጅት ለማከናውንም ሆነ ዘር ለመዝራት በቂ የሆነ እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተጨማሪም የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት በጥቂት በምስራቅ በሚገኙ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተገኘው አንስተኛ የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል ግን በጥቂት አካባቢዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት የነበረ ቢሆንም በሰብሎች እድገትም ሆነ በእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ የጎላ አሉታዊ ተጽዕኖ አልነበረዉም (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው አዋሽ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌና ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገጸ ምድር የውሃ ሽፋን ይዞት አግኝተዋል። ይህም ሁኔታ በየተፋሰሶቹ በሚገኙ ግድቦች፣ ሰው ሰራሽ የውሃ መያዥያዎች እንዲሁም የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር የውሃ አቅምን ከማጎልበት ጥሩ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡

## 2. መግቢያ


በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ሙሉ በሙሉ ያዳርሳል፡፡ በጁን በመደበኛው ሁኔታ የሚታየው የዝናብ መጠንና ስርጭት የተሻለ መልክ የሚኖረው ከወሩ አጋማሽ ጀምሮ ነው። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ15-24 ቀናት ያህል ይዘንባል። ይሁንና በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ30-100ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ3-16 ቀናት ያህል ይዘንባል። ከክረምት ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በጁን የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች እስከ 30% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ። በመደበኛ ሁኔታ የጁን ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በይበልጥ እየተጠናከሩ የሚሄደበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የዝናቡ ስርጭት የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.1 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በጁን የሶስተኛዉ አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 5)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆንና፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ደግሞ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ. ከጁን 21-30, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ (ከ1-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 5)፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን

| ክልል | ዞን | የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ፣ ቦረና | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞኖች የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | የሰሜን እና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ባስኬቶ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ፋፈን፣ ኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አፋር | ጥቂት የደቡብ አፋር ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በጁን የሶስተኛዉ አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በአፋር ክልል፣ በሰሜን ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሊይ ከ29 እስከ 41 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡





ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 21-30, 2025
የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ የመጀመሪያው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛው እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡



ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

በመጪዎቹ የጁላይ መጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)። ከዚሁ ጋር በተያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን፣ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

## 2.5 እ.አ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራል፡፡ ስለሆነም የሚኖረው እርጥበትም ለወቅቱ የእርሻ ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፣ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞኖች የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም<br>ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ወስጥ እርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገትና የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል<br>• ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት | • የአፈር እርጥበት መብዛት፣ የማሳዎች መጨቅየት እና የውሃ መተኛት<br>• ውሃ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የማሳ ዝግጅት ማከናወንና ዘር መዝራት<br>• የውሃ ማንጣፈፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ከወዲሁ ማዘጋጀት<br>• የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>• የእርሻ ድግግሞሽን መቀነስ |
| የሰሜን እና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን<br>• ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል<br>• ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት | • ከፍተኛ ትነነት በሚኖርባቸዉ አካባቢዎች መጠነኛ የሆነ የአፈር ዉስጥ እርጥበት መኖር<br>• የሰብሎች የውሃ ፍላጎት አለመሟላት | • የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን<br>• የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለበልግ ሰብሎች ፍሬ ማፍራት<br>• ለመኸር ግብርና እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የሚኖረው እርጥበት ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን<br>• ደረቅ ሰሞናት መኖር | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር የማሳ ዝግጅትና የዘር መዝራት ማከናወን<br>• የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን<br>• የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |
| የሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ቀድመው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት<br>የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | • ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት | • ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች ላይ የእርጥበት መብዛት እና ውሃ በሰብሎች ላይ መተኛትን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ይህንን ለመከላከል የሚያስችሉ የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በጊዜ መሰብሰብ |
| **በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ፣ ቦረና አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ባስኬቶ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ፋፊን፣ ኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ፣ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለተዘሩ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር<br>• ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• የሚኖረውእርጥበት በመድረስ ላይ ላሉ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን | የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.6 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለተፋሰሶቹ የውሃ አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አስር ቀናት በተፋሰሶቹ የሚኖረውን እርጥበት በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ለመቀነስ ከታች በሠንጠረዥ የተመላከቱትን የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| አብዛኛው የላይኛው እና የመካከለኛው<br>• ኦሞ ጊቤ<br>• ስምጥ ሸለቆ<br>• ባሮ አኮቦ<br>• አዋሽ<br>• ተከዜ<br>• አባይ<br>አብዛኛው የላይኛው<br>• ገናሌ ደዋ<br>• ዋቤሸበሌ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል<br>• የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መሻሻል<br>• በሁሉም አካባቢ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን መሻሻል | • የደለል ስጋት መጨመር<br>• የውሃ ብክለት ስጋት መጨመር<br>• | • የጎርፍ የፍሳሽ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት<br>• የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |
| የመካከለኛው እና የታችኛው<br>• አዋሽ<br>• ገናሌ ደዋ<br>• ዋቤሸበሌ<br>• ኦጋዴን | መጠነኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል<br>• የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • ከፍተኛ ትነት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት<br>• ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ እጥረት | • የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል መጠቀም<br>• ወራጅ የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውሃ የማሰባባሰብ ማጠራቀም |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው ታችኛው<br>• ኦጋዴን፣ አይሻ<br>• መረብ ጋሽ<br>• አዋሽ<br>• ገናሌ ደዋ<br>• ዋቤሸበሌ<br>• ኦጋዴን | ደረቅ ሁኔታ | • የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር | • የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት መቀነስ<br>• | • የውሃ እጥረት በሚገጥማቸው አካባቢዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ<br>• የሚገኘውን ውሃ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተዳደር<br>• የገጸ ምድር የውሃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et